# ባርነት ባደባባይ

አማራው በማንነቱ ላይ እየደረሰበት ያለውን ጥፋት ለመቋዋቋዋም በጎንደር ወያኔ ላይ ሲያምጽ ብ አ ዴ ን እንደተለመደው ፈጣሪን ከማገልገል ይልቅ እንደሱ ለመ ቀሌው አምባገነን መንግስት ያደሩትን የኦርቶዶክስ ቄሶች ጎኑ ሻጥ አድርጎ ሕዝባዊ ትግሉ እንዲኮላሽ ሲያዝገዝትና ሲያስለምን መሰንበቱ የአደባባይ ሚስጢር ነው። ሁኔታው እንዲቀዛቀዝ ሕወሀት ባወጣው ስልት በፌደራል መንግስት በኩል ያው ሁሉም የሰለቸውና ጥርስ አልባው ብ አ ዴ ን የአማራ ክልል ም/ፕሬዝዳንት የሚ መራ ቡድን ከ ጎንደር አማራ ሕዝብ ሽማግሌዎች ጋር ድርድር የሚሉትን የጉዶች ጉድ ከተያያዙት ፍሬ ከርስኪ በሆኑና ኢላማውን በሳተ ጉዳይ ላይ ዙሪያ ጥምጥም ሲሄዱበት ሳምንት አስቆጥሮአል፡ በውይይቱ ሽማግሌዎቹ ራሳቸው ለችግሩ መነሻ በሆነው በትግሬዎች ቅኝ በተያዙት የአማራ መሬቶች ላይ መወያየት አጀንዳቸው አድርገው መውሰድ እንዳለባቸው ቢያውቁም ላካባቢው ሕዝብ ግልጽ ባልሆነ መ ንገድ " ሰላምና ልማት " በሚል የገዢው ጥቅም ዙሪያ ላይ አተኩረው ግዜያቸውን እያባከኑ እንደሆነ በሁኔታው ቅር ከተሰኙ ተሳታፊዎች ወሬ ሾልኮ ወጥትዋል።

ብናልፍ አንዱዋለም ወያኔ ስልጣን ላይ ሲመጣ ከሂሳብ አስተማሪነት በአዲሱና በረ ከት ተመልምሎ ወያኔን የተቀላቀለና ባጭር ግዜ ከፍተኛ የፓርቲና ክልል አመራር የሆነ አፍቃሪ ሕወሀት የሆነ ግለሰብ ነው፡ ለብዙ አመቶች የት/ት ቢሮ ሀላፊነትን ይ ዞ አማርኛ እንዲዳከም ከመቀሌ የሚደርሰውን ትዛዝ እያስፈጸመ የሚገኝ ጻረ አማራ ወንጀለኛም ነው፡ በአማራው ክልል አማርኛ በ 12 ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እንዳይ ካተት የወሰነው እርሱ ነው። በላስታ ወረዳ ሕዝቡ አማራ መሆኑ እየታወቀ ት/ት በ ዋግ አገውኛ እንዲሰጥም በጉልበት ተማሪዎችን ያልሆኑትን እንዲሆኑ በማስገደድ ላይ ያለ እባብ ነው፡ ታዲያ የሱ ጌታ ወያኔ በሰሜን ጎንደር አማርዎች ላይ በግድ ትግሬዎ ች ናችሁ ብሎ ቢያስገድድ ምን ይገርማል፡ ባንድ ወቅት በአማራ ቲቪ ሲናገር " አማ ርኛን የማይናገሩ የክልሉን ማህበረሰብ አካል ሙብት ለመጠበቅ ሲባል በ 12 ኛ ክፍ ል ፈተና እንዳይካተት ወስነናል " ብሎ ባይናውጣነት ትንሽ እንክዋን ሳያፍር የተናገረ ባንዳ ነው።

ይሄ ሰውዬ ዛሬ የጎንደር አማራን ትግል ገና በእንጭጩ ዞፍ ብሎ እንዲወድቅ ሽማግ

ሌዎቹ አይናቸውን ኢንቨስትመንት ወደሚስቡ ጉዳዮች እንዲያዞሩ ሲወተውታቸው ሰንብትዋል፡ በመካከሉም ወደ ትግራይ የሄዱት መሬቶች ሕገ መንግስቱን መሰረት ባደረገ መንገድ እንጂ በተቃዋሚና በሽብርተኞች በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ እንዳልሆ ነም ተረት ተረት የላምበረት እያላቸው ይገኛል፡ በቀናት መበራከት መዘናጋት የሚ ታይባቸው ሽማግሌዎችም በድርድሩ መዳከማቸው ቀስ በቀስ በመታየት ላይ ይገኛ ል፡ ይህ ደግሞ ለወልቃይትና ጠገዴ ታጋዮች ብቻ ሳይሆን ለመላው አማራ እጅግ በጣም አስከፊ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡ ለምሳሌ አልተዘጋጀንም የሚል ምክንያት የተሰጠውና ሳይደረግ የቀረው ሰላማዊ ሰልፍ ከዚሁ ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ጥርጥር ሊገባን አይችልም፡ አሁን ላይ በሚቀጥለው እሁድ ይደረጋል የሚ ል ዜና ቢሰማም ወያኔ ባህርዳር ላይ ሁለት የዳያስፖራ በአሎችን ስለሚያከብር ለደ ህንነት ሲባል ለሌላ ግዜ ተላልፎአል የሚል ዜናም ነገና ተነገዲያ ብንሰማ አይደንቀን ም፡ በዚሁ ድርድር ላይ ብናልፍ የጎንደርን ከንቲባ በማዘዝ ሰልፉን ማስከልከሉ መታ ወስ ያለበት ጉዳይ ነው።

በእንደዚህ አይነት ድርድር ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ እንደሚባለው ወያኔ አቋዋሙ ን ሳይቀይር ብ አ ዴ ንም ከባሪያነት ሳያመልጥ የሽማግሌዎቹ ግዜ ማባከን የተቀጣጠ ለውን የአማራ ጸረ ወያኔ ትግል ወደ ትቢያ ሊወረውረው ስለሚችል የጎንደር አማራ የሆናችሁ ከመስመር ሳትወጡና ነገ ተነገዲያ ሳትሉ ያደባባይ ትግሉን ማቋዋረጥ አይ ኖርባችሁም፡ የሽማግሌዎቹ ነገር ልክ እንደ ቄሶቹ ሊሆን ይችላል፡ ወያኔ እንክዋን አገ ር ቤት ውጪ ያለውንም ሆዳም በገንዘብ እየገዛ ተላላኪው የማድረግ ልምድ ያለው አደገኛ ዘንዶ መሆኑን አትርሱ፡ ብ አ ዴ ን እንደሆነ ለይቶለታል! ከእንግዲህ ወዲህ ከወቀሳና ምክር ተምሮ እንደስሙ አማራ ይሆናል ብላችሁ የምታልሙ ካላችሁ እር ማችሁን ብሉ! ፓርቲው ወደ መጨረሻው የእንጦርጦስ ጉያ ተውዘግዝጎና ዳግም ላይ መለስ ገደል ገብትዋል፡ ምሳሌ ልስጣችሁ በአውሮፓና አሜሪካ ወዘተ. ያሉ የወያኔ ደጋፊ ትግሬዎች በትግሬ ንብረቶች ለደረሰው ጥፋት የአማራ ክልል ካሳ መክፈል አለ በት ብለው ሲወተውቱ እነ ደመቀ መኮንን፤ ብናልፍና አለምነው ወዘተ. ሳይውሉና ሳ ያድሩ ካሳ ባደባባይ ክልሉን አስከፍለዋል፡ ግን እነኚህ አፍቅሮ ወያኔዎች አማራው በ መላው ኢትዮጵያ መጤ ተብሎ ሲመታና ንብረቱን ሲቀማ አንዲት የመቆርቆር ስሜት አድሮባቸው አያውቅም፡ እንዲያውም እንክዋን ካሳ ሊያሰጡት ይቅርና ጭራሽ " ማን ሰው አገር ሂድ አለው. . . " እያሉ አማራውን የበለጠ ሲያስጠቁት የኖሩ አሞተ ቢስ ባንዶች ናቸው።

ልብ ካላችሁ የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ እንደሚባለው እነዚህ አሻንጉሊቶች ለትግሬዎቹ ሲከራከሩ "ሕገመንግስቱ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተዛውረው የመኖርና ንብ ረት የማፍራት መብታቸው ተከብሮላቸዋል. . . " ስለዚህ በየግዜው አማራውን እ ያፈናቀሉ በመተማ፤ በቁዋራ፤ በአርማጭሆና ሌሎችም ቦታዎች የክልሉ ገበሬ አንዲ ት ሄክታር መሬት ማረስ በተሳነው ዘመን ለትግሬዎቹ በመቶና በሺህ የሚቆጠር መ ሬት በኢንቨስትመንትና ልማት ሽፋን እየሰጡ ያካባቢው አማራ አናሳ ሰፋሪው ትግ ሬ ደግሞ በዝቶና ሀብት አፍርቶ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ጭራሽ ወደ ትግራይ መካተት አለብን የሚል ጥያቄ እስከማቅረብ እንዲደርስ ያደረጉና አማራውን እንደ ካንሰር እያስገዘገዙ ያሉ ካድሬዎች ናቸው፡ ታዲያ ሕገ መንግስቱ ከጥፋት ውጪ ለአማራው ምን የፈየደው አለው? 1/በኢትዮጵያ ባሉ ነገዶች አስከዶታል 2/መጤና ነፍጠኛ አስብሎ አስመትቶታል 3/ጥሮ ግሮ ያፈራውን ንብረት አስወድሞበታል የተረፈውን ያለ ካሳ አስቀምቶታል 4/በዜግነቱ ከቦታ ቦታ ተዛውሮ የመኖርና ንብረት የማፍራት መብቱን ነጥቆታል 5/ ዳር ድንበርዋን ለማስከበር ደሙን ባፈሰሰላትና አጥንቱን በ ከሰከሰላት አገር የበይ ተመልካችና ቤትስኪያን እንደገባች ውሻ ተቅበዝብዞ የሚኖር ስደተኛ አድርጎታል 6/ጽንፈኛ፤ ሽብርተኛና ትምክህተኛ አስብሎ ፈርጆታል ወዘተ.

በጎንደር የተቀሰቀሰውን የአማራ የነጻነት ተጋድሎ ማስቀጠል ካስፈለገ ቄስ ገዝቶኛል፤ ሽማግሌዎች ተደራድረው መብቴን ያስከብሩልኛል፤ ብ አ ዴ ን አሁን ላይ ገብቶታል ወዘተ. በሚሉ ነገሮች መዘናጋቱን እርግፍ አድርጎ በመተው በኦሮሚያ ሕዝቡ በእንቢ ተኝነት ተቃውሞውን እንደቀጠለ ሁሉ በወልቃይት የአማራ ማንነት ኮሚቴ የተቀጣ ጠለው የአማራ የነጻነት ችቦ እንዳይጠፋና ጤዛ ሆኖ እንዳይቀር ሕወሀትንና ብ አ ዴ ንን ለመጣል ያላሰለሰ ትግል ባደባባይ የተለያዩ ተቃውሞዎችን በማድረግ የአለም ዜ ናና መነጋገሪያ ሆኖ የአማራው የነሳነት ደውል እንዲሰማ መዘናጋትን እርግፍ አድርገ ን ማንነታችን ከምድረ ገጽ ከመጥፋቱ በፊት ያለምንም ማቅማማት ጠላቶቻችንን እንፋለማቸው! ! !

አብነት ሁነኛው ነኝ!